# ምዕራፍ ሁለት
# ሳይንስን መገንዘብ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት አካላትን ትጠራላችሁ፡፡
- የስሜት አካላትን በመለየት ጥቅማቸውን ትናገራላችሁ፡፡
- የስሜት አካላት ያላቸውን ዝምድና ትለያላችሁ፡፡
- የግል ንጽሕናን በመረዳት ትተገብራላችሁ፡፡
- የጨለማን ምንነት ትገነዘባላችሁ፡፡

## የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

2.1 የሰውነታችን ክፍሎች

2.2 የግል ንጽሕናን መጠበቅ

2.3 የብርሃን ምንነት

# 2.1 የሰውነት ክፍሎች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት አካላትን ትጠቅሳላችሁ፡፡
- የስሜት አካላትን በመለየት ጥቅማቸውን ትናገራላችሁ፡፡
- የስሜት አካላት ያላቸውን ዝምድና ትለያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች
- የስሜት አካላት

## ሀ. የሰውነታችን ክፍሎች ምንነት




ሥዕል 2.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

## ተግባር አንድ

**የተግባሩ ዓላማ**፡- ውጫዊ የአካል ክፍሎችን መናገር

**መመሪያ**፡- ተራ በተራ እየተነሳችሁ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን እያመለከታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ተማሪዎች! ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

**ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚባሉት**፡- ፀጉር፣ ራስ፣ ግንባር፣ ጆሮ፣ ዓይን፣ አፍንጫ፣ አፍ፣ አንገት፣ ትከሻ፣ ደረት፣ ሆድ፣ ክንድ፣ እጅ፣ ጉልበት፣ እግርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## የቡድን ውይይት አንድ

**የውይይቱ ዓላማ**፡- ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን መዘርዘር

**መመሪያ**፡- አራት አራት በመሆን ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን ማድረግ ስለሚገባን ጥንቃቄዎች በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## መልመጃ 2.1

**የሚከተለውን ጥያቄ አንብባችሁ መልሱ፡፡**

1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ዘርዝሩ፡፡

## ለ. የስሜት አካላትና ጥቅሞቻቸው

ተማሪዎች! ቀጥለው የቀረቡትን ሥዕሎች አስተውላችሁ ተመልከቱ፡፡



ሥዕል 2.2 የስሜት አካላት

አምስቱ የስሜት አካላት የምንላቸው ፡-

- ዓይን
- አፍንጫ
- ጆሮ
- ምላስ እና
- ቆዳ ናቸው፡፡

## የቡድን ውይይት ሁለት

**የውይይቱ ዓላማ**፡- የአምስቱን የስሜት አካላት ተግባር መናገር

**መመሪያ**፡- ከላይ በሥዕል 2.2 ውስጥ የሚገኙ የአምስቱን የስሜት አካላት ተግባራት ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ከየቡድናችሁ አንድ አንድ ተማሪ በመወከል መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡



ሥዕል 2.3 የስሜት አካላት ጥቅም

ሰንጠረዥ 1 የስሜት አካላትና ጥቅማቸው

| ተ.ቁ | የስሜት አካላት | ጥቅም |
|---|---|---|
| 1 | ዓይን | ለማየት |
| 2 | ምላስ | ለመቅመስ |
| 3 | አፍንጫ | ለማሽተት |
| 4 | ጆሮ | ለመስማት |
| 5 | ቆዳ | ለመዳሰስ |

ዓይን፣ ምላስ፣ አፍንጫና ጆሮ ከአንገት በላይ የሚገኙ ሲሆን ቆዳ ግን አብዛኛውን ውጫዊ የአካል ክፍላችንን የሚሸፍን ነው፡፡ ሁሉም የስሜት አካላት በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን ለመረዳት ስለሚያስችሉ ዝምድና አላቸው፡፡

## መልመጃ 2.2

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አንባባችሁ ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1.ራስ ውጫዊ የአካል ክፍል ነው፡፡

2.አፍንጫ ለማሽተት ይጠቅማል፡፡

3.የስሜት አካላት ጥቅም የላቸውም፡፡

4.አምስቱም የስሜት አካላት ዝምድና አላቸው፡፡

5.ለመቅመስ የሚጠቅመው የአካላችን ክፍል ምላስ ነው፡፡

# 2.2 የግል ንጽሕናን መጠበቅ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- የግል ንጽሕናን በመረዳት ትተገብራላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃል**

- ንጽሕና

### የግል ንጽሕና ምንድን ነው?

የግል ንጽሕና ማለት ዘወትር የሰውነታችንን፣ የፀጉራችንን እና የምንለብሳቸውን ልብሶች ንጽሕና መጠበቅ ነው፡፡







ሥዕል 2.4 የግል ንጽሕና አጠባበቅ

ተማሪዎች! ከሥዕል 4 ምን ተረዳችሁ!

ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችንን ንጽሕና ለመጠበቅ፡-

1. እጆቻችንን፣ እግሮቻችንን እና ፊታችንን ዘወትር በውሃ እና በሳሙና መታጠብ
2. በየጊዜው ፀጉራችንን በውሃ እና በሳሙና መታጠብና ማበጠር
3. ቢያንስ በሳምንት ሁለት ቀን ገላችንን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ
4. ዘወትር የአፍንጫችንን እና የጆሮቻችንን ፅዳት መጠበቅ እና ጥፍራችንን መቁረጥ ይኖርብናል፡፡

**የግል ንጽሕናችንን ካለመጠበቅ :-**

- ለሕመም እንጋለጣለን
- ሰዎች ሊያገሉን ይችላሉ
- በሌሎች ሰዎች ላይ ሕመምን እናስተላልፋለን
- ጠረናችን ሌሎች ሰዎችን ምቾት ያሳጣቸዋል

## ተግባር ሁለት

**የተግባሩ ዓላማ**፡- የግል ንጽሕናን በመረዳት መተግበር

**መመሪያ**፡- ተማሪዎች! አንድ ቀን መርጣችሁ በትምህርት ቤታችሁ በሰልፍ ሥነ-ሥርዓት መርሐግብር ላይ የእጅ ንጽሕና አጠባበቅን በተግባር አሳዩ፡፡

የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-

- ሳሙና
- ውሃ
- የእጅ ማስታጠቢያ እቃ

## መልመጃ 2.3

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ መልሱ።**

1.የግል ንጽሕናችንን እንዴት እንጠብቃለን?

2.የግል ንጽሕናችንን አለመጠበቅ ምን ጉዳት አለው?

# 2.3 የብርሃን ምንነት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- የጨለማን ምንነት ትገልጻላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- ብርሃን
- ጨለማ

ሀ.



ለ.



ሥዕል 2.5 የጨለማ እና የብርሃን ልዩነት

## የቡድን ውይይት ሦስት

**የውይይቱ ዓላማ**፡- የብርሃንን እና የጨለማን ምንነት መገንዘብ

**መመሪያ**፡- አምስት አምስት በመሆን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

1. ብርሃን ምንድን ነው?
2. ጨለማ ምንድን ነው?
3. አንድን ነገር በግልጽ ማየት የሚቻለው በብርሃን ወይስ በጨለማ ነው?

## ተግባር ሦስት

**የተግባሩ ዓላማ**:- የብርሃንን እና የጨለማን ልዩነት መግለፅ

**መመሪያ**:- ተማሪዎች! ዓይናችሁን ስትጨፍኑ የሚታያችሁን ነገር ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ብርሃን** ነገሮችን ለማየት የሚረዳ የጉልበት ዓይነት ነው። ብርሃን ከሌለ ነገሮችን ማየት አንችልም። ስለዚህ አንድን ነገር በግልፅ ማየት የሚቻለው ብርሃን ሲኖር ነው።

የብርሃን ጉልበት ሲያንስ ነገሮችን እንዳንመለከት የሚያደርግ ክስተት ጨለማ ይባላል።

### መልመጃ 2.4

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ነገሮችን ማየት የምንችለው ብርሃን ሲኖር ነው።

2. በጨለማ ነገሮችን ማየት አንችልም።

3. ብርሃንና ጨለማ ተመሳሳይ ናቸው።

# ማጠቃለያ

- ራስ፣ ጆሮ፣ ዓይን፣ አፍ፣ አንገት፣ ትከሻ፣ ደረት፣ ሆድ፣ እጅ፣ እግር እና የመሳሰሉት ውጫዊ የአካል ክፍሎች ናቸው::
- ዓይን፣ አፍንጫ፣ ምላስ፣ ጆሮ እና ቆዳ የስሜት አካላት ናቸው::
- ሁሉም የስሜት አካላት የራሳቸው የሆነ ተግባር አላቸው::
- ውጫዊ የአካል ክፍሎቻችንን ከሚጎዱ ነገሮች መጠንቀቅ አለብን::
- ውጫዊ የአካል ክፍሎቻችን ንጽሕና መጠበቅ ይኖርብናል::
- ብርሃን ነገሮችን ለማየት የሚረዳ የጉልበት ዓይነት ነው::
- የብርሃን ጉልበት ሲያንስ ነገሮችን እንዳንመለከት የሚያደርግ ነገር ጨለማ ይባላል::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ።**

1. ዓይን የስሜት አካል ነው፡፡
2. ብርሃን ነገሮችን ለማየት ያስችለናል፡፡
3. እግር ውጫዊ የሰውነት ክፍል ነው፡፡
4. የግል ንጽሕናችንን መጠበቅ አለብን፡፡
5. ሁሉም የስሜት አካላት አንድ ዓይነት ተግባር አላቸው፡፡

**ለ. በ “ሀ” ሥር የተጠቀሱትን የስሜት አካላት ሥዕል በ “ለ”ሥር ከተጠቀሱት ጥቅማቸው ጋር አዛምዱ።**

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| 1. |  | ሀ. ለመስማት |
| 2. |  | ለ. ለማየት |
| 3. |  | ሐ. ለመዳሰስ |
| 4. |  | መ. ለማሽተት |
| 5. |  | ሠ. ለመቅመስ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አንብባችሁ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1.ውጫዊ የሰውነት ክፍል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አፍንጫ ለ. ጆሮ ሐ. ሁሉም

2.የስሜት አካላት ስንት ናቸው?

ሀ. ሦስት ለ. አራት ሐ. አምስት

3.ለመዳሰስ የሚጠቅመው የስሜት አካል የቱ ነው?

ሀ. ምላስ ለ. ቆዳ ሐ. አፍንጫ

4.የግል ንጽሕናችንን አለመጠበቅ በሌሎች ሰዎች ላይ ምን ጉዳት ያስከትላል?

ሀ. በሽታ እናስተላልፋለን

ለ. ጠረናችን ምቾትን ያሳጣል

ሐ. ሁሉም

5.ነገሮችን በግልፅ ለማየት የሚያስችለን የቱ ነው?

ሀ. ብርሃን ለ. ጨለማ ሐ. አፈር

## ፍተሻ

የምታውቋቸውን ተግባራት በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን "✓" ምልክት አድርጉ፡፡

አጥጋቢ የመማር ብቃት

1. ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት አካላትን እጠራለሁ፡፡ ☐
2. የስሜት አካላትን በመለየት ጥቅማቸውን እናገራለሁ፡፡ ☐
3. የስሜት አካላት ያላቸውን ዝምድና እለያለሁ፡፡ ☐
4. የግል ንጽሕናን በመረዳት እተገብራለሁ፡፡ ☐
5. የጨለማን ምንነት እገነዘባለሁ፡፡ ☐